# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 6

እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 7

እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕና ........ 8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 9

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ........ 9

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ 9

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ ከፍተኛ ዝናብ በሚ.ሜ. ........ 9

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10

እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11


# እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በማርች ሁለተኛው አሥር ቀናት በከባቢ አየር ውስጥ የነበረው እርጥበታማ የአየር ሁኔታ በተሻለ መልኩ በመጠናከሩ በአብዛኛው የሀገሪቱ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ተስፋፍቶ ታይቷል። በተለይም በመካከለኛው፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ እንደነበር ከሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የተሰበሰቡ የዝናብ መረጃዎች ያሳያሉ። በመሆኑም ዝናቡ በመጠን በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች መሙላት ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተከታታይነት ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች መካከል በጭፍራ 104.0፣ 51.0፣ 42.0 እና 30.4፣ በአዲስ አበባ 41.4፣ 31.0፣ 51፤ በዳሊፋጊ 88.0፣ በቡርጂ 34.8፣ በአማን 62.6፣ ሜጋ 35.0፣ በወላይታ ሶዶ፣ 40.3፣ 45.5 እና 49.3፣ በወሊሶ 35.6፣ በሰመራ 46.0፣ በዱብቲ 71.0፣ በሻምቡ 35.5፣ በሳውላ 71.1፣ በነቀምቴ 56.2፣ በሚሌ 50.0፣ በሞያሌ 43.5 እና 32.8፣ በመኢሶ 50.0፣ በሙተሃራ 33.0፣ 37.6፣ በምዕራብ አባያ 44.0፣ በቀብሪደሃር 30.0 እና 44.8፣ በደገሀቡር 31.1፣ በገዋኔ 30.4 እና 34.0፣ በፊቅ 150.0፣ 130.0 እና 94.3፣ በገለምሶ 36.2፣ በኤሊዳር 30.7፣ በእነዋሪ 36.0፣ በዱብቲ 71.0፣ በዲላ 30.8፣ በዶሎመና 30.5፣ በድሬዳዋ 33.4፣ በቦሬ 82.0፣ 32.1 እና 33.0፣ በብላቴ 45.1፣ በቡኢ 45.5፣ በባቲ 32.0 እና 35.0፣ በአዋሽ አርባ 55.0፣ በአደሌ 39.2፣ በሀሮማያ 36.6፣ በአቦምሳ 48.4፣ እንዲሁም በያቤሎ 66.5፣ በሚ.ሜ. ይጠቀሳሉ፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች የነበረው የሙቀት መጠን አንፃራዊ መጨመር ያሳየ ሲሆን፤ ከ40 ዲግሪ ሲልሸየስ በላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በጎዴ 42.2፣ በፉኚዶ 41.0፣ በኤሊያ 40.0 ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከአማራ በዋግህምራ፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ከጋምቤላ የማጂንክ ዞን፤ አብዛኛው የአፋር ክልል፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ ከቄሌም ወለጋ በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ5-379 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በዋግህምራ፣ በምስራቅ ጎጃም፣ ደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ከጋምቤላ የማጂንክ ዞን፤ በአፋር፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ ከቄሌምና ከምዕራብ ወለጋ በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ የተቀሩት አብዛኛው የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     ኢ.ሌ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ሁለተኛዉ አስር በመካከለኛው፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአመዛኙ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደነበረና ከዚህም ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እና የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው። እንዲሁም በብዙ የሃገሪቱ አካባቢዎች በ24 ሰዓት የተመዘገበው ከባድ ዝናብ በተለይም ውሃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረ ቢሆንም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች መሙላት ሊያስከትል በመቻሉ በእንሰሳት፣ በሰዎችና በንብረት ላይ እንዲሁም ቀደም ብለው በተዘሩትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙት ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች ከ40 ዲግሪ ሲልሽየስ በላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን የተመዘገበ ሲሆን ከዚሁ የሙቀት መጠን መጨመር ጋር ተያይዞ በእነዚህ አካባቢዎች ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንሰሳት መኖና ውሃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## ኢ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች የሁለተኛው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተሻለ መልኩ በመጠናከሩ በአብዛኛው የሀገሪቱ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ተስፋፍቶ ታይቷል። በተለይም በመካከለኛው፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ተፋሰሶች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል በአብዛኛው ኦሞ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽ፣ የላይኛው እና መካከለኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ የላይኛው እና የታችኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጠበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደ ነበራቸው መረዳት ተችሏል፡፡ በተገኘው ከፍተኛ እርጥበት የጎርፍ ክስተትም ነበረው፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄደው ከማርች አጋማሽ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በማርች ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት አብዛኛዎቹን የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ ቦታዎችን በሸፈነ መልኩ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይስተዋልባቸዋል፡፡

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በአሁኑ ወቅት በድርቅ ተጽዕኖ ስር በሚገኙት በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተስፋፉና እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በልግ አብቃይ በሆኑ ሥፍራዎች የበልግ ወቅት ዝናብ ያገኛሉ፡፡


በአጠቃላይ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣አርሲና ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፣ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፤ ሐረሪ ክልል፤ ድሬ ዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከጋምቤላ የማጃንግ ዞን፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከትግራይ ክልል የደቡብና የምሥራቅ ትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3፣ 4 እና 5፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ ክልል አብዛኛው ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተነሳ በምስራቅ አማራ፣ በሰሜንና ደቡብ አፋር፣ በነገሌ ቦሬ፣ በዶሎመና፣ በሜጋ፣ በያቤሎ፣ በሞያሌ እንዲሁም በጥቂት የሶማሌ ክልል ዞኖች ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ። በሌላ በኩል የሀገሪቱ ቆላማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 ድግሪ ሴልሽየስ በላይ የሙቀት መጠን እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2023 የሚኖረዉ ከፍተኛ ዝናብ በሚ.ሜ.

## እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኃላ ከወቅታዊ የእርጥበት ሁኔታ መጠናከር ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አምራች በሆኑ አካባቢዎች የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ በስፋት የሚከናወንበትና አስቀድመው የተዘሩ የበልግ ሰብሎች በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ የሚደርሱበት ሲሆን፤ በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የማሳ ዝግጅት የሚደረግበት እና በአንዳንድ አካባቢዎችም ዘር የሚዘራበት ወቅት ነው፡፡

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት የሚጠበቀው የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት አስቀድመው ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና በየአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለተለያዩ የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በአርብቶ አደሮችና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችም የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜንና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል ጎን ለጎን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሀ ጉድጓዶችን ከማጎልበት አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በሌላ መልኩ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አንዳንድ አካባቢዎቸ ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጎርፍ ሊፈጠር ስለሚችል አርሶ አደሮች ጎርፎችን መደበኛ መፋሰሻቸውን ተከትለው እንዲፈሱ የማድረግ ተግባራትንና ከከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚፈጠረው የጎርፍ ውሃ በረባዳማ አካባቢዎች ጉዳት እንዳያደርስ የውሃ ፍሰት ፍጥነትን የሚያዳክሙ ተግባራትን አስቀድሞ ለማከናወን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም አንዳንድ አካባቢዎች ከሚጠበቀው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በተለይ ውሃ ገብና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃውን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ ውሃውን በቀላሉ ማጠንፈፍ በሚችሉበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ቢመቻች ሊደርስ የሚችለውን ችግር መቀነስ ያስችላል። በተጨማሪም ለዘር የተዘጋጁ ማሳዎች በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ የሚገባ ቢሆንም በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ውሃን የመሰብሰብና የማጠራቀም ተግባራት ማጠናከር እና እርጥበት አጠርና ከፍተኛ የውኃ ትነት ያለባቸው አካባቢዎች የውሃ ብክነትን ለመከላከል የሚያሰችሉ ዘዴዎችን ሊተገብሩ ያስፈልጋል፡፡

# እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የማርች ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት የደቡብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ይኖራቸዋል፡፡፡ከዚህም ተፋሰሶች በአብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦጋዴን፣ የመካካለኛ እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛዉ ባሮአኮቦ፣ አፋር ደናክል እና በጥቂት የመካከለኛዉ አባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከላይ በተጠቀሱ ተፋሰሶች የሚገኘው ከፍተኛ እርጥበት ለውሃ ሀብት አዎንታዊ ጎን ቢኖረውም፤ለጎርፍ መንስኤ ሊሆን ስለሚችል ለጎርፍ ተጠቂ በሆኑ የተፋሰስ ክፍሎች በንብረት እና በሰው ህይወት ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡፡በሌላ በኩል የተቀሩት የሰሜን እና ሰሜን ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡